ጳጉሜን

ጳጉሜን የሚለው ስያሜዋ “ኤፓጉሜኔ” ከሚለው የግሪክ ቃል የመጣ ሲሆን ትርጉሙ ጭማሪ ማለት ነው። በግእዝ ተውሳክ ማለት ሲሆን ተውሳክ ማለት ተጨማሪ ማለት ነው። “ወሰከ - ጨመረ” ከሚለው የግእዝ ግስ የተገኘ ነው። ከኢትዮጵያ ውጭ ያሉ ሌሎች ሀገሮች ጳጉሜን የወር ተጨማሪ ያደርጓታል። ይኸውም ይታወቅ ዘንድ እኛ የወርን ቁጠር 30 ስናደርግ እነርሱ 31 ብለው የሚቆጥሩት ወር አላቸው። ይኹን እንጂ ኢትዮጵያውያን ሊቃውንት ጳጉሜን የወር ተጨማሪ ሳያደርጉ የዓመት ተጨማሪ አድርገዋታል።

ጳጉሜን በዓመቱ መጨረሻ ላይ አምስት ወይም ስድስት ቀን በመሆን ትመጣለች። በአራት ዓመት አንዴ ማለትም በዘመነ ሉቃስ መጨረሻ በዘመነ ዮሐንስ መግቢያ ጳጉሜን ስድስት ቀን ትሆናለች። በዚህም ሀገራችን ኢትዮጵያ የአስራ ሦስት ወራት ጸጋ /Thirty months of sunshine/ በመባል ትታወቃለች። ጳጉሜን ስድስት በምትሆንበትም ጊዜ ጾመ ነቢያት /የገና ጾም/ ህዳር 14 ቀን ይገባና ታህሳስ 28 ቀን ጾሙ ተፈትቶ የልደት በዓል ይከበራል።

በቅድስት ቤተክርስቲያን ካሉት ሁለት የፈቃድ አጽዋማት መካከል አንዱ በዚህ በጳጉሜን ወር የምንጾመው የፈቃድ ጾም ነው። ይህም ጾመ ዮዲት በመባል ይታወቃል። ይህ ግን እንደ አንደኛው የፈቃድ ጾም /ጽጌ ጾም/ በብዙዎች ዘንድ የታወቀ አይደለም።

የዮዲት ጾም የሚባለውም እርሷ ስለ ጾመችው ነው። እዚህ ላይ ዮዲት ተብላ የተጠቀሰችው በቤተክርስቲያን ታሪክ ትምህርት ላይ በጥፋት ሥራዋ በተደጋጋሚ የምትጠቀሰው ዮዲት ጉዲት እንዳልሆነች ለማሳወቅ እንወዳለን። ወደ ታሪኩ ስንመለስ የፋርስ ንጉስ ናቡከደነጾር በሠራዊቱ ተመክቶ ሹም ጠላት አጥፋ ድንበር አስፋ ካመነው እጅ መንሻ እየተቀበልህ ያለመነውን እያሳመንህ ና ብሎ ለጦር አበጋዙ ለሆሎፎርኒስ ትዕዛዝ ሰጠ። ዮዲ 2፥2-7። እርሱም እንደታዘዘው በኃይላቸው የታመኑ 12 ሺህ እግረኞችንና በፈረስ የተቀመጡ 12 ሺህ ጦረኞችን እየመራ ዘምቶ ካመነው እጅ መንሻ እየተቀበለ ያለመነውን እያሳመነ ብዙ ሀገሮችን እያጠፋ ሲሔድ ከአይሁድ ከተማ ደረሰ በዚህም ብዙ ጥፋት በመድረሱ የእስራኤል ልጆች አለቀሱ።

ዮዲት ባሏ ሞቶባት ከወንድ ርቃ ንጽሕናዋን ጠብቃ በጾም በቀኖና በህዘን ተወስና ትኖራለች በተፈጠረው ጥፋት ህዝቡ ላይ ለመጣው መከራ ማቅ ለብሳ በራስዋ ላይ ትብያ ነስንሳ ወደ እግዚአብሔር አለቀሰች። የፍጥረቱን ጥፋት የማይሻ እግዚአብሔር አምላክም ሕዝቡን የሚያድኑበትን መንገድ ለመጠየቅ ሱባኤ በገባች በሦስተኛው ቀን ገለፀላት። ዮዲ 8፥2። ከዚህ በኋላ ጠላታቸውን በዮዲት ምክንያት እስራኤላውያን እስከ ዮርዳኖስ እየተከተሉ አጥፍተዋቸዋል።

ዮዲት ጠላቷን ለማጥፋት የቻለችው በጾምና በጸሎት ከእግዚአብሔር አምላክ ኃይል አግኝታ ነው። ስለዚህ ምዕመናን ጥንተ ጠላታችን ሰይጣንን ፈቃደ ሥጋን ለማሸነፍ በጾም ከፈጣሪያችን ኃይልን መጎናጸፍ አለብን ብለው ጳጉሜን በፈቃድ ይጾማሉ።

የጳጉሜን ወር ዕለተ ምጽአት የሚታሰብባትም ወር ነች። ይህም ጳጉሜን የዓመታት መሸጋገሪያ ጨለማው የክረምት ወቅት ወደ ማብቂያው የምናልፍባት እንደሆነች ሁሉ ምጽአትም ከጊዜያዊው ወደ ዘላለማዊ ከምድራዊ ወደ ሰማያዊ ከዚህ ዓለም ወደ ወዲያኛው መሸጋገሪያ ነውና።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር

▭▭▭▭▭▭▭▭▭

ዩቲዩብ ቻናላችንን **SUBSCRIBE** በማድረግ አገልግሎቱን ይደግፉ።

https://www.youtube.com/channel/UCDFE-5zWnDAIS8UxfM8RAdA/featured?view_as=subscriber

@Orthodox_Tewahdo_bot
@Wengelin_Lehzbachin †

@Wengelin_Lehzbachin †

▭▭▭▭▭▭▭▭

ጳጉሜን እንዴት እናሳልፍ ?



1. ተርቤ ነበርኩ አበላችሁኝ

❖ለተቸገሩ ሰዎች የምናደርገውን በጎ ስጦታ(ቁራሽ እንጀራ) ያመለክታል።

❖የተቸገሩ ወገኖች በየቤተክርስቲያኑ በየመንደሩ በየአስፋልቱ በየጥጉ ወድቀው ይገኛሉና። ስመ እግዚአብሔርን በመጥራት ይማፀናሉ።

❖በሌላ በኩል ደግሞ ምዕመናን የእግዚአብሔርን ቃል ከመስማት ተርበዋልና። ከቅድስት ቤተክርስቲያን ጡት ወተቷን የቀመሰ ሁሉ የተማሪውን ማስተማር ይጠበቅበታል። ማቴ 4፣3 ዘዳ 8፣3

❖እንዲሁም የክርስቶስን ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም መቀበል ፈልጎ ተርቦ ይሆናል።



@Orthodox_Books

ወንጌልን ለህዝባችን ቲዩብ

2. ተጠምቼ ነበር አጠጣችሁኝ




❖ቀዝቃዛ ውሃ ያጠጣ በችግሩ ጊዜ የረዳ ዋጋ አለው ማለቱ ነው። ጌታም በወንጌሉ ቀዝቃዛ ውሃ የሰጠ ዋጋው አይጠፋም። ብሏል ማቴ 10፣42።

❖ስለዚህ ካህናት የምእመናንን ፍላጎት ማርካት **ከሥጋው** ማብላት **ከደሙ** ማጠጣት ግዴታቸው ይሆናል።

❖የተጠማ ሰውነት በንፁህ ውሃ ደረቁን ሰውነት ማጠጣት ማለምለም ተገቢ ነውና። ሥጋ ያለውሃ ነፍስም ያለ ቃለ እግዚአብሔር አይኖርም።ዮሐ 7፣38





@Orthodox_Books

ወንጌልን ለህዝባችን ቲዩብ


3. ስደተኛ ነበርኩኝ ተቀበላችሁኝ




❖እንግዳ በሚችሉት አቅም ማስተናገድ ተቀብሎ ማሳደርን ያመለክታል። በቤተክርስቲያናችንም ዘወትር ይነገረናል። በሀገራችን ልማድ፣ በባሕል ቤት ለእንግዳ፣ ቤት የእግዚአብሔር ነው እየተባለ ይነገራል።



❖ስደተኛ ከላይ ጥላ ከታች ጫማ ከፊት ከኋላ እቅፍ የሚያደርጋቸው ዘመድ አዝማድ የላቸውም እና ለሀገር ለሰው ባዳ ናቸውና ስደተኛን መቀበል ለክርስቲያን ወጉና ክብሩ ነው።








ወንጌልን ለህዝባችን ቲዩብ






4. ታርዤ ነበርኩ አለበሳችሁኝ

- እግዚአብሔር አምላክ በፈቀደ ሁለት እጀ ጠባብ ያለው አንዱን ለሌለው ወገኑ እንዲሰጥ ያስተምረናል።
- ሰው ካልለበሰ ከእንሰሳት ያንሳልና። ፀጋውን ክብሩንም ያረክሳልና ለታረዙ ማልበስ ፀጋን መጎናፀፍ ነው።
- አዳም በሀጢአቱ ከፀጋው ታረዘ እኛ በሀጢአታችን መታረዝ እንዳይኖርብን ከቅድስት ቤተክርስቲያን አባቶች **የንስሀ ልብስ በወንጌል** ተመርተን እንልበስ እናልበስ።
- ከቃሉ የታረዘን ብዙ ነንና እርቃናችንን እየተጓዝን የሰው መሳቂያ መሳለቂያ መሆንና ሥነ ምግባርን ልብስ አድርገን መልበስ አለብን።

@Orthodox_Books ወንጌልን ለህዝባችን ቲዩብ

5. ታምሜ ጎበኛችሁኝ

@Wengelin_Lehzbachin


❖ሰው የሆነ ሁሉ ለታመመ ወንድሙ በጎ አድራጎት መፈፀም አለበት።

❖ይህንን አመጣችሁልኝ ይህንንና ይህንን ሰጣችሁኝ አላለም። ነገር ግን አቅሙ በፈቀደው ማዕናናት በሀሳብ፣ በገንዘብ በሌሎችም እንድንጎበኛቸው በሽተኞችኝ እግዚአብሔር ይማርህ ማለት ምግባቸው ነውና።

❖በየፀበሉ በየሆስፒታሉ በየቤቱ የአልጋ ቁራኛ፣ የደዌ ዳኛ ሆነው መጻጉን የመሰሉ አሉና። በሌላም በኩል ቃሉን አጥተው በነፍስ ታመው ይሆናል ቃለ ሕይወት ወንጌልን ለታመመው ነፍስ መስጠትና በቃሉ ማዕድነት መጠየቅ ተገቢ ነው።

ወንጌልን ለህዝባችን ቲዩብ

6. ታስሬ ነበርኩ ወደኔ መጣችሁ

ወንጌልን ለህዝባችን ቲዩብ

❖የታሰረን መጎብኘት ማነጋገር ችግኑን ጠይቆ ተረድቶ ለማቃለል መሞከር ትልቁ ክርስቲያናዊ ተግባር ነው። እናም የታሰሩትን ወገኖች መጠየቅ ይገባል።

❖በየእስር ቤቱ የሚሰቃዩ ሰዎችን እግዚአብሔር ያስፈታህ ብሎ መጠየቅ ተገቢ ነው። በነፍሳችንም የታሰርን ብዙ ነንና በሀጢያት ገመድነት ሰንሰለት የፊጢኝ የታሰርን አለንና በቃሉ አስፈቺኝት ልንጠያየቅ ይገባል።

❖የበረታው የደከመውን በመጠየቅ ከሀጢያት እስር ልንፈታ እንችላለን።






subscribe በማድረግ ቤተሰብ ይሁኑ!
https://www.youtube.com/channel/UCDFE-5zWnDAIS8UxfM8RAdA/featured?view_as=subscriber

JOIN ➤ **@Orthodox_Books**
JOIN ➤ @Orthodox_Books